# ቅኔና አዘማሪ


ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com



መስከረም ፳፻፯ ዓ.ም.

http://www.medhanialemeotcks.org/


## መግቢያ

ለአዘማሪ ሙያ ተስማሚ የግብር መግለጫ መሆን ያለበት የቱ ነው? አዘማሪ ወይስ አርቲስት? በሚል በአቶ ዓለም ነጻነት ሬድዮ የቀረበው ውይይት ለዚህች ጦማር መነሻ ሆኖኛል።

ከቀደሙ አባቶች እንደሰማሁት አዘማሪ ብቻውን የቆመ አይደለም። ከብዙ ነገሮች ጋራ ከቅኔያችን፣ ከዜማችንና ከስሜታችን ጋራ የተያያዘ ነው። አዘማሪ የሚለውን ቃል ከነዚህ ነጥሎ ለማቅረብ መሞከር ያዘማሪን ክብርና ቦታ ዝቅ ያደርገዋል የሚል ስጋት አለኝ።

ስለዚህ አዘማሪ ወደሚለው ቃል ዘው ብለን ከመግባታችን በፊት የአዘማሪን ተልእኮ መዳሰስ ሊኖርብን ነው። አዘማሪ የሚለው ቃል የግብሩ (የተልእኮው) መግለጫ ነው። ተልእኮውም ራሱ አዘማሪ ተቀኝቶም ሆነ ገጥሞ ወይም ሌላ የተቀኘውን በዝማሬው ቅላጼ ከጉሮሮውና ከመሳሪያ ጋራ አስማምቶ፣ ቀምሞና አስወድዶ አስውቦ ለህዝብ ማቅረብ ነው። ህዝቡንም ከባህሉ ከታሪኩ ከኢትዮጵያዊነቱ ከስሜቱም እርስ በርሱ የበለጠ ያጣብቃል። እርስ በርሱ ያቀራርባል። ያዋህዳል። ያስተባብራል። እንደ ኢትዮጵያ ከመሰለ በቅኝ ግዛት ሳይወረር የራሱን ጠብቆ ከሚኖር አገር የሚፈልቅ አዘማሪ የሚያስተላልፈው ቅኔ፦ ኅብር፤ ሰምና ወርቅ፤ ሰረዝ፤ ጎዳና፤ ውስጠ ወይራና ሌላም ዓይነቶች አሉ። ያዘማሪን ክብርና ቦታ ዝቅ ላለማድረግ ስለአዘማሪ ከመናገሬ በፊት ስለኢትዮጵያዊ ቅኔ ትንሽ ማብራሪያ መስጠት ፈለኩ።

## ቅኔ

በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ (ቅኔ) ህግ እያንዳንዱ የቅኔ ስንኝ (ግጥም)፤እንደ ሰውነታችን ነፍስ (ምሥጢር) ይኖረው ዘንድ እንደ ሰውነታችን በሥጋ፣ በጅማት፣ በደም ባጥንት መጋጠም አለበት፤ ወይም ህይወት ያለው ሰው ይኖርበት ዘንድ በመሰረት በግርግዳ በምሰሶና በጣራ እንደ ቤት መጋጠም አለበት። ግጥም የሚባለው በተመሳሳይ ፊደል ማለቁ ብቻ አይደለም። ገጠመ ወይም ቤት መታ የሚባለው በነዚህ በመሰራቱና በአስረጅና በምሳሌ ተደግፎ በአራት አውታሮች፤ በስድስት አእማድ ተሰርቶ ሲቀርብ ብቻ ነው።

በፈጣሪና በተፈጥሮ መካከል ያለውን ኩነት፣ ክንውንና ሂደት የሚገልጽ ነው። አዲሱ ትውልድ፤ ሰውነቱን ሥጋውን፤ ደሙንና ነፍሱን ካለፈው ትውልድ ወርሶ ይመጣል። ወኔውን፣ ነጻነቱን፣ ባህሉን፣ እምነቱን፣ ታሪኩንና ስሜቱን ካለፈው ትውልድ የሚወርሰው ግን በቅኔ ነው። ቅኔ ከቤተ ሰብ፤ ከጽዋዕ ማህበር፣ እስከ መንግስታዊ አስተዳደር ያለውን ይዘት መሰረት አድርጎ፤ ያለፈውን ዘምንና ትውልድ አሁን ከሚኖርበት ዘመን ጋራ እያነጻጸረ ለወደፊቱ ትንቢታዊ ራእይ የሚያሳይ መነጽር ነው። የፈጣሪን ከሃሊነት፣ የተፈጥሮን ውበትና ከንቱነት ለሰሚው ድህንጻ መንፈስ (ተመስጦ) በአራት አውታሮች በስድስት አዕማድ ተጠርቦ ለዝቦ ለስልሶ ተጌጦና ተውቦ ይቀርባል። አራት አውታሮችና ስድስት አዕማድ የተባሉት የሚከተሉት ናቸው።

## አራት አውታሮች የሚባሉት፡-

- ፩ኛ፡- "ወላዴ ሕይወት፣ ርእሱ ለአእምሮ፡ መዝገበ ጥበብ" እያልን በኪዳናችን የምናደንቀው የቅኔ ምንጭ የሆነውን ተፈጥሮ፣ የፈጠረ የሰራ አምላክ ነው።

- ፪ኛ፡- በውበቱና በኃላፊነቱ የቅኔ ማሕጸን የሆነው ተፈጥሮ ነው።

- ፫ኛ፡- የፍጥረትን ውበት አቀነባብሮ የሚያቀርበው ባለ ቅኔ (የቅኔ ሸማኔ)

- ፬ኛ፡- በህብረተ ሰቡ ጣእመ ዜማ ቅኔን አስጊጦና አስውቦ ለቅኔው ባለቤት ህዝብ አቅርቦ፣ ህዝቡን በፈለገው መንገድ ለማዘመር ለማሰራት ለማደራረግ የሚያቀርብ ባለሙያ (አዘማሪ) ነው።

## ስድስት አዕማድ የሚባሉት፡-

፩ኛ፡-አድራጊ፣

፪ኛ፡-ተደራጊ፣

፫ኛ፡-ተደራራጊ፣

፬ኛ፡-አደራራጊ፣

፭ኛ፡-አስደራጊ፣

፮፡-አስደራራጊ፤ ናቸው።

ከላይ ከተዘረዘሩት ከስድስቱ አእማድ ሶስቱ ማለትም፡- አድራጊ፣ተደራራጊና አስደራጊ የሌሉት አምላክ ብቻ ነው።

አስረጂ፡- "ዘቦቱ ኩሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ" (ዮሐ ፩፡፫) እንደተባለው፤ አምላክ ሁሉን ፈጣሪና አድራጊ ነው። አቻ የለውም። ከሱ በላይም ምንም ስለሌለ አስደራጊ የለውም። ተወዳዳሪ የሌለው አንድ ብቻ አምላክ በመሆኑም ተደራራጊ አይደለም። እነዚህ ሶስት አእማድ፤ አምላክን አይመለከቱም። በሰማይም በምድር ያለ ሁሉ ፍጥረት ከመጀመሪያው ከአድራጊነት በቀር በተዘረዘሩት አውታሮችና አዕማድ ድንኳን ውስጥ የተካተተ ነው።

ከቤተ ሰብና ከጽዋዕ ማህበራት ጀምሮ እስከ መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ፤ ከላይ ከተዘረዘሩት ስርዓቶች ውጭ አንድ አካል ካፈነገጠ፤ ~~(ተወዳዳሪ)~~ የሌለኝ አድራጊ፣ ፈጣሪና አደራራጊ እኔ ብቻ ነኝ ማለት ነውና፣ በጊዜው ካልተስተካከለ ለማረም ከባድ፤ ላካባቢው ሁሉ ሀውክ ይሆናል።

እነዚህን አእማድ ሳያውቅ ማንም ሰው ከድርጅታዊ አሰራር መግባት ይቅርና ከትዳር መግባት የለበትም ይላሉ አባቶች። ትዳር፤ ማኅበር፤ ድርጅትም ሆነ አገር የሚፈርሰው የእነዚህን ምሥጢር መረዳት አቅም የሌለው ሰው በግንባር ቀደምነት ለመምራት ሲሰለፍ ነው።

ይህን ለማስረዳት አባቶች ብዙ የሚጠቅሷቸው ማስረጃዎችና ምሳሌዎች አሏቸው። ጽሑፌን ለማሳጠር ወደ አባቶች ምሳሌዎች መሻገሬን ትቼ፤ ሩቅ ሳንሄድ ወያኔ በኢትዮጵያ ላይ ያደረሰውን ጉዳት በስድስቱ የቅኔ አእማደ ምሥጢር ብንመለከተው፤ አስረጅነቱ ተገቢና ተስማሚ ይመስለኛል።

## አስረጅ

ወያኔ ተወዳዳሪ የሌለው አድረጊና ፈጣሪ ሆኖ፣ መራጭም አስመራጭም፣ ተመራጭም ሁሉንም እኔ ነኝ አለ። ብቸኛ አድራጊ፤ አደራራጊ፣ አስደራጊና አስደራራጊ ሆኖ መጣ። ኢትዮጵያን ገነጠለ፣ አስገነጠለ፣ አስገነጣጠለ፣ አገነጣጠለ። አንዱን ጎሳ ከሌላው ጎሳ በድንበር በቋንቋ ለየ፤ ለያየ፤ አለያየ። እራሱ እየለያየ ገደለ፤ እርስ በርሱ አጋደለ፤ አስገደለ፤ አገዳደለ፤ አስገዳደለ። ከሱ በውቀት በሞራል የተሻሉትን ያገር ሽምግሌዎችን፤ የተማሩትንና ጋዜጠኞችን በሀሰተ ክሰሰ፤ አስከሰሰ፤ አካሰሰ፤ ራሱ በሀሰተ መሰከረባቸው፤ አስመሰከረባቸው፤ አመሰከካረባቸው። ራሱ ዳኛ ሆኖ ፈረደባቸው፤ ጠበቃም ሆኖ አስፈረደባቸው። የህዝብ ሀብት በዘበዘ፤ በካድሬዎቹ አስበዘበዘ፤ መሬቱን ከኢትዮጵያውያን ነጥቆ፤ ቀምቶና አዋርዶ ከውጭ አገር ጋብዞ ላመጣቸው ሰዎች አሳልፎ በመስጠቱ፤ ኢትዮጵያውያንን

እንዲያዋረዱ አስደረጋቸው። በኢትዮጵያ ህዝብ አስጠላቸው አጣላቸው። እንዲጥላሉ አደረጋቸው፤ አስደረጋቸው፤ አደራረጋቸው። በምርጫ ሲሸነፍ የህዝቡን ድምጽ ዘረፈ፣ አዘረፈ፣ አዘራረፈ፤ ገደለ፣ አጋደለ፣ አስገደለ፣ አገዳደለ። ከስህተትህ ታረም ያሉትን ሁሉ፡ አራሚ ነኝ። በማንም አልታረምም። ተወዳዳሪ የሌለኝ አስተራራሚ እንጅ ተራራሚም አይደለሁም አቻ የሌለኝ አራሚ ነኝ፤ በማለት የአምላክን ቦታ ወሰደ። ዘግይቶ መገለጹ ባይቀርም ህዝብ በቀላሉ የማይደርስበትን ደባ ስለገለጡበት ብቻ የሀገር ጠላቶች ናቸው ብሎ ጠልቶ በህዝብ አስጠላ፤ አጥላላ፤ አጠላላ፤ አስጠላላ። ይህን ደባ በህይወት በሌሉት አባቶች ላይም ሳይቀር ፈጸመው።

ለምሳሌ፦የሰው አካል ቆራጭ ናቸው ተብለው በታሪካችን የሚከሰሱት አባታችን አጼ ዮሐንስ እንጅ፤ አባታችን አጼ ምንይልክ አልነበሩም። ወያኔ እነ አቶ ገብረ ኪዳን ደስታን በመሳሰሉ ካድሬዎች የአርሲን ልጆች የናቶቻችሁን ጡት የቆረጡ ናቸው ብሎው ስለ አጼ ምን ይልክ አስተማረ። እርስ በርሱ እንዲማማር አደረገ አስደረገ። ይህንኑ የሀሰት ታሪክ የሚገልጽ ሀውልትም አንዲሰሩ ቀሰቀሳቸው፤ አነሳሳቸው፤ አስተባበራቸው አሰራቸው። *[በነገራችን ላይ አቶ ገብረ ኪዳን ማለት የኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለወያኔ ጥፋት መፈጸሚያ ማስፈጸሚያ እንድትሆን እንድትዳከም እቅድ ዘርግቶ አስመሳይ ቆሞሳትን መነኮሳትን ጳጳሳትን እየመለመለ ለመላክ እቅዱን ካወጡት አንዱ ነው። ዝርዝሩን ለማንበብ ከፈለጉ ይህን* [የነ ፋሴቅ ወጥመድ] *] የሚለውን ይጫኑ ።*

ኢትዮጵያውያንን እርስ በርስ የሚያጣላ የሚያራራቅ የሚለያይ ሀውልትም እንዲሰሩ ካደረጓቸው በኋላ፤ በተለመደው ሸፍጡ ጀርባውን ለኦሮሞ ፊቱን ለቀረው ህዝብ አዙሮ "እነዚህ ጠባቦች ኋላ ቀሮች ሀውልት ሰሩ እያሉ" ለአማራው፤ ለጉራጌው ለአፋሩና ለቀረው ሁሉ ጎሳ ኦሮሞዎችን አምቶ፤ አስጠልቶ፤ አጣልቶና አጥላልቶው አቀረባቸው።

በእውቀት፣ በማስተዋልና በብሄራዊ ፍቅር ከወያኔዎች እጅግ የመጠቀው ንጹሐ ኢትዮጵያዊ ቴወድሮስ ካሣሁን የሚባለው ባለ ቅኔ (አዘማሪ) "ጥቁር ሰው" በማለት ባቀረበው ቅኔ ለዘመናት ወያኔ ሲተበትበው የኖረውን አገዳዳይ አጨራራሽ ቅኔ፤ ባንዲት ዝማሬው ባንዲት ቀን ከንቱ አረገባቸው ማለትም መላ ኢትዮጵያውያንን በራሱ በወያኔ ላይ ገለበጠበት።

ወያኔ፤ በባቄላ አውድማ ገብታ ባቄል ለቅማ መብላት የለመደች ዝንጀሮ፤ በጤፍ አውድማ ገብታ ጤፍ መልቀም ሲያቅታት "ጤፍ የዘራ ገበሬ ስራ ያጣ ነው" አለች እንደምትባለው ዝንጀሮ ሆነ።

በተገቢው መንገድ መቋቋም ያቃተው ወያኔ፤ እንደ ቴድ አፍሮ ያሉትን አዘማሪዎች "ትምክህተኞች" በማለት አምቶ፣ ጠልተው፣ አስጠልተውና አጥላልተው ለኦረሞው ህዝብ አቀረበው። ከዚያም ርቆ በመሄድ ነፍሰ ገዳይ ብሎ፤ በራሱ ጥብቅና አስከስሶ በራሱ ዳኝነት በራሱ ፍርድ ቤት ራሱ ከሶ፣ ፈርዶ አስፈርዶ አፈራርዶ አሰረው አሳሰረው።

ይህም ብቻ አይደለም፤ በአርሲ ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖችን በሰይፍ አረደ፣ አሳረደ፤ አስተራርደ። ቀጠለን በቦታው እንዳልነበረደ እንዳላወቀና እንዳልሰማ፣ እንዳላረደ እንዳላሳራደና እንዳላስተራረደ መስሎ ቀረበ። ቀጠለና ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ፤ አማራውን ከኦረሞው ጋራ፤ የበለጠ ለማፋጀትና ለማገዳደል ኃላፊነቱን በአርሲ ኦሮሞ ሙስሊሞች ላይ አሸከመ።

የትግራይን ህዝብ ከቀረው ወገኑ ለመቁረጥ ለማስቆረጥ ለማቆራረጥ የአክሱም ሀውልትና የአደዋ ድል የትግራይ ህዝብ ብቻ ነው። የኢትዮጵያዊነትን ብሔራዊ ስሜት ለማጥፋት ታሪክን ባህልንና ስሜት የምታንጸባርቀውን ሰንደቅ አላማ አቃጠለ፤ አስቃጠለ። የኢትዮጵያን ህዝብ ከኢትዮጵያውነቱ አስጠልቶ ለማስበረገግ ጎቦ ሽማኔ መሳይ አርማ የለጠፈበትን አስበርጋጊ ባንዲራ ተከለ። አስተከለ።

ይህ ሳያንሳቸው ከነሱ ክልል ውጭ በሆነው የነሱ ባልሆነው በሁመራ መሬት በአባይ ወንዝና በሚመረተው ነገር ሁሉ አድራጊ፣ ፈጣሪ፣ አደራራጊና አስደራራጊ ሆኖው ቁጭ አሉ።

የኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ በውጭ ሰወች የተጻፈው ታሪክ ጨካኝ ሰው ቆራጭ አድርጎ የሚከሳቸው አጼ ዮሐንስን ነው። አጼ ምንይልክን እንኳን የናቶችን ጡት ቆራጭ አርጎ ሊያቀርባቸው ይቅርና እንደ አጼ ዮሐንስ እጅ ቆረጡ አላላቸውም። የኢትዮጵያውያ ህዝብ ለሁሉም ተመሳሳይ ክብር በመስጠት ሁሉንም አባቶቻችን ናቸው በማለት አይወቅስም አይከስም እንጅ፤ ነገሩ ተነስቶ ከአማራው ስሜት ጋራ አያይዞ አመራውን ለመጎዳት ለማስጎዳት ለመጥላት ለማስጠለት ተብሎ በዚህ አስቀያሚ መንገድ ከቀረበ አማረው የወያኔን አፍ የሚዘጋ የሚያዘጋና የሚያዘጋጋ አእማደ ምሥጢር አለው።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ "ዐጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት" በሚል ርእስ በገጽ 458 ላይ እንደመዘገቡት፤ አጼ ምንይልክ ስንኳን የወገናቸውን ጡት ሊቆርጡ፤ "ሁሉም እንደ ሃይማኖቱ ይኑር ባይና የካቶሊክ ሃይማኖት ያለውንም ፈረንጅ የሚያቀራርቡ ናቸው" ይላል። አጼ ምንይልክ ይከሰሱ ይወቀሱ ከተባለ በዚህ ብቻ ሊሆን በተገባ ነበር።

በአጼ ዮሐንስ ሠራዊት ውስጥ ተሰግስገው የነበሩት የነ ገብረ ኪዳን ደስታ አባቶች የጥንት ወያኔዎች ማለት ነው፣ አጼ ዮሐንስንና አጼ ምንይልክ እርስ በርስ ለማዋጋት ለማጣላት ሁለቱንም በህዝብ ለማስጠላት፣ የትግራይን ህዝብ ከቀረው ህዝብ ጋራ ለማጋደል "ይህን ሁሉ ከኛ የበለጠ ወታደር ይዘው እንዴት አይዋጉም? ለምን ለአጼ ዮሐንስ ይገብራሉ? እያሉ፣ አጼ ዮሐንስን ከአጼ ምን ይልክ፣ ያጼ ምንይልክን ሠራዊት ከአጼ ዮሐንስ ሠራዊት ጋራ፣ የትግራይን ህዝብ ከቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋራ ያጋጩ እንደነበረ ሰፍሯል። በገጽ 459 ላይ የሰፈረውን ይመልከቱ።

ይህን መርዝ ይነሰንሱ የነበሩት የነ አቶ ስብሀት ነጋ አውራሽ የሆኑት ወያኔዎች ከአጼ ዮሐንስ ጋራ ተባብረው የእስላሞችን እጅ እንደ ቀረጡና እንዳስቀረጡ፣ አጼ ምንይልክን ከኦረሞው ህዝብ ለማጋጨት፣ የኦሮሞውን ህዝብ በወቅቱ ይመሩ የነበሩትን እነ ፍታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን ከራሳቸው ከኦሮሞው ህዝብ ጋራ ለማጋጨት፣ ወደ አርሲ ሰርገው ገብተው የሰው እጅ በመቁረጥ ልማዳቸው በአርሲ የነበሩትን የእናቶችን ጡት ቆረጡ አስቆረጡ ለምን አይባልም?

የዘመናችን ወያኔዎች ካባቶቻቸው በወረሱት ሰይጣናዊ ባህርያቸው፣ በየክልሉ ሰርገው በመግባት ሰውን ምድሩን በመቁረጥ በማቆራረጥ በማስቆረጥ ላይ ናቸው። አሁን እያደረጉ ያሉትን ተግባር ቀድሞ ካደረጉት ተግባራቸው ጋራ ንጽጽር ውስጥ አስገብተን እንድናይ አጼ ዮሐንስን ሳይቀር በተቃራኒ ሚዛን ውስጥ እንድናሰልፋቸው እያደረጉ ናቸው። በዚያ ዘመኑ የነበሩትን ወያኔዎች አሁን ካሉት ወያኔዎች ጋራ አነጻጽሮ የራሱን ግንዛቤና ትዝብት እንዲወስድ የኢትዮጵያን ህዝብ አስገድደውታል። የኢትዮጵያን ህዝብ ከዚህ እስከፊ ትዝብት ላይ ካደረሱ በኋላ፣ ወያኔዎች ይህን ሳይጣናዊ ስራቸውን እንዲያቆሙ ሲጠየቁ፣ እራሳቸውን በትግራይ ህዝብ ላይ ጠምጥመው በመቅረብ በራሳቸው ላይ የሚወረወረውን ክስና ጥላቻ ወደ ትግራይ ህዝብ እያለበሱ በመቀስቀስ የትግራይን ህዝብ ከቀረው ወገኑ እየለዩት እየቆረጠት እየለያዩት እየቆ ራረጡት፣ እያላያዩትና እያቆረረጡት ነው።

ወያኔዎችን በሰይጣናዊ ውርስ ብክለታቸው የፈለጉትን ቢያደርጉ የመላ ኢትዮጵያውያን ጠላትነታቸውን የበለጠ እያከረረው ከመሄድ በቀር፣ የኢትዮጵያ ህዝብ አይለያይም፣ አይቆራረጥም። በነሱ የተለያየውም ተለያይቶ አይቀርም። እንደነ አባ ማትያስ ያሉትን መሳሪያዎቻቸውን ያሰማሩባት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የወለደቻቸው ሊቃውንት አበው ዘመናቸውን ዋጅተው ያለፉትን ሁለቱንም አባቶች አጼ የሐንስንም አጼ ምንይልክንም እኩል እንድንወዳቸው ከዚህ በታች በጠቀስኩት አብራርተው አስተምረውናል።

ቅዱስ አትናቴዎስ "ኦ አዳም ወሔዋን እስመ አኮ ዘይትከሀል ኪያክሙ ንጽዐል በከመ ለልሳን ዘኢይትከሀል ይጽዐልዎ እንዘ ይትናገሩ ቦቱ። ወከማሁ አንትሙ ንሕነ፡ ወንሕነ አንትሙ" (መ ቅ፣ቁ ፴፩) ብሎ ነበር። ሲተረጎም "አዳምና ሄዋን ሆይ! እናንተ ባመጣችሁብን ፍዳ ብንሞት ብንፈርስም እናንተን ለመውቀስና ለመክሰስ እንደበት የለንም። እኛም ከናንተ የተሻልን አይደለንም" ማለት ነው። አትናቴዎስ የተናገረውን ምሳሌና አስረጅ በማድረግ፣ ከትግሬም፣ ከኦሮሞም፣ ከጉራጌም፣ ከአፋርም፣ ከአማራም ከወላይታውና ከሁሉም ዘር የነበሩበትን ዘመናቸውን እየዋጁ ያለፉትን አባቶቻችንን ከመውቀሳችን፣ ከማስወቀሳችን፣ ከማወቃቀሳችን በፊት፣ ራሳችን በዘመናችን የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በቅኔዎቻችን አእማድ እንድንለካ አስተምረውናል።

"አንተ ከነሱ የተሻልክ ካልሆንክ በህይወት የሌሉትን አባቶች እየጠቀስክ፣ አንተ የምትጠላውን በመውቀስ ሙት ወቃሽ፣ የምትወደውን በማወደስ ሙት አንጋሽ እንዳትሆን ተጠንቀቅ" እያሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሊቃውንት አበው ሲያስጠነቅቁ ሰምቻለሁ።

የዘመናችን ወያኔዎች እነ አቶ መለሰ በአጼ ዮሐንስ ዘመን ከነበሩት ሙታን ወያኔዎች አባቶቻቸው በወረሱት አስደራጊ አደራራጊና አስደራራጊ ባህርያቸው እስኪሞቱ ድረስ የፈጸሙት ደባ አልቆም ብሎ፣ አቶ መለሰና አባ ጳውሎስ ከሞቱ በኋላ የተተኩ ወያኔዎች ውርሱን ከነ አቶ መለሰና አባ ጳውሎስ የተቀበሉት በመንግስት አመራር እነ አቶ ሥዩም በረከት፣ በቤተ ክርስቲያናችን እነ አባ ማትያስ እርስ በርሳችን በማደባደብ ቀጠሉበት። ከሞቱት አባቶቻችን ጋራም እያደባደቡን ነው። ኢትዮጵያን ሊመሩ ቀርቶ ገና ገቢር ተገብሮ መለየት ያልቻሉ ናቸው

ወያኔዎች በቀጥታ በሚቆጣጠሯቸው የመንግስትና መንግሥታውያን ያልሆኑ ድርጅቶችን ይቅርና፣ በክርስትና እምነት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋራ፣ በኦርቶዶክሳዊነት ከምሥርቅ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ፣ በነገረ መለኮትና በቀኖና ከምትመስላቸው ከኦሬንታል ጋራ ባላት ግንኙነት ብዙ ታዛቢ ያላትን ኦርቶድሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን ሳይቀር፣ ያለምንም ይሉኝታ የራሱ መሳሪያ በማድረግ ፍላጉቱን ማድረጊያ ማደራረጊያ፣ ማስደረጊያና ማስፈጸሚያ አድርጓታል።

አቡነ ማትያስ በማነኛውም መስመር ችሎታና ብቃት እንደሌላቸው በግልጽ እየታወቀ፣ለወያኔ ማደረጊያ ማስደረጊያ ማደራረጊያ ምቹ በመሆናቸው ብቻ፣ "ተወዳዳሪ የሌለኝ ብቸኛ ቅዱስ አዋቂ ችሎታው ያለኝ ነኝ" እያሉ በድፍረት እንዲቀረቡ አድርጓቸዋል። የአባ ማትያስን ለወያኔ አስደራጊነትና አስደራራጊነት ምቹነት ከዚህ በታች እንመልከት።

# አባ ማትያስ የወያኔን ጥፋት አስደራጊ፣አደራራጊ፣ አስፈጻሚና አፈጻጻሚ ናቸው።

የተፈፀሙባቸውን ቦታቸው የሚከተሉት ናቸው::

- ፩ኛ:-በዲሲ መድኃኔዓለም
- ፪ኛ:-በከንሳስ ኪዳነ ምህረት
- ፫ኛ:-በሲኖዶስ
- ፬ኛ:-በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ላይ በተቃራኒ የፈጽሟቸውን ያስፈጸሟቸውንና ያፈጻጸሟቸውን ከዚህ በታች እንመልከት።

፩ኛ:- የዲስ መድኃኔ ዓለምን ህዝብ ከሰሱ፣ አስከሰሱ፣ አካሰሱ። ተጣሉ፣አጣሉ፣አጠላሉ፣አጥላሉ። ምእመናኑ የሰበሰቡትንም ገንዘብ ለጠበቃ ከፈሉ፣ ነዋየ ቅድሳቱንም አከፋፈሉ፣ አካፈሉ፣አስከፈሉ።

፪ኛ:- አቻዎቻችን አብያተ ክርስቲያናት የማይቀበሉትን፤ ሊቃውንት አበው የሚጸየፉትን የቅድስት ድንግል እመቤታችንን ሰብእና የሚነካውን፤ የጌታችንንም ፍጹም ትስብእት አቃውሶ የተዋህዶ እምነታችንን የሚያቃውሰውን የተሳሳተ ትምህርት ከንሳስ ኪዳነ ምህረት ውስጥ በመክተታቸው፤ "ጳጳስ አይሳሳትም አይዋሽም" የሚል ከንቱ ግምት ያላቸውን ሰዎች አሳሳቱ፤ አሳቱ። ከፈሉ። ለዩ።ለያዩ፤ አለያዩ። በጠበጡን፣ አበጣበጡን፣ ከፈሉን፣ አከፋፈሉን፣ አጣሉን፣ አጠላሉን፣ በተኑን፣ በታተኑን፣ አበታተኑን። ክደው አስካዱ፣ አከዳዱ።

በእውቀት በችሎታ ከሳቸው የላቁት ካህናት "ተሳስተዋል ወደ ከንሳስ ተመልሰው ስተው ያሳሳቱትን፤ የከፋፈሉትን

ያለያዩትን ህዝብ ይቅርታ ጠይቀው ያዋህዱት ያስማሙት" ቢሏቸው፤ ራሳቸውን አቻ ተወዳዳሪ የሌሽ አድርገው አቀረቡ። ለዚህ ማስረጃ ከፈለጉ አባ ሰረቀ "እውነትና ንጋት" በሚል ርእስ አዘጋጅተው ያቀረቡትን በቤተ ክህነት ተመርቆ ለህዝብ የቀረበውን መጽሐፍና የከንሳስ መድኃኔዓለምን ድረ ገጽ ይመልከቱ።

፫ኛ:- አባ ማትያስ ለሲኖዶስ መከፋፈል ሙሉ በሙሉ ምክንያት ናቸው ባንልም። ወያኔ የፈጠረው መከፋፈል ተገቢ አለመሆኑን ስላወቁ አስታራቂ ሆነው ቀርበው ነበር። በመጨረሻም አቡነ ጳውሎስን "ከፋፋይ" በሚል ዘልፈዋቸው እንደነበረ ሁሉም ያውቀዋል።

አቡነ ጳውሎስ ከከፋፋዩ ከወያኔ ጋራ የነበራቸው ግንኙነት በግብራቸው እስከ ተገለጠ ድረስ ወደ ፓትርያርክነቱ ሲመጡ አባ ማትያስን የገጠማቸው ተቃውሞ አቡነ ጳውሎስን አልገጠማቸውም። የሁለቱን አመጣጥ በቤታችን ቅዱሳት መጻሕፍት ስንመዝነውም፤አቡነ ጳውሎስ ከመጡበት መንገድ ይልቅ አባ ማትያስ የመጡበትን መንገድ እጅግ የከፋ ይሆነል።

አቡነ ማትያስ ራሳቸው በሽምግልና የጀመሩት የሁለቱ ሲኖዶሶች እርቅ ሳይፈጸም፤ የፓትርያርክነት ምርጫ እንዳይደረግ፤ ማንም እንዳይቀበለ የሚባለውን ችላ ብለው ፤ ለማስታረቅ የተሰለፉትን ቡድኖች ይሰቀሉ በማለት አስፈራርተው የበተኑትን የእነ አቶ ስብሀት ነጋን አመራር በመከተል "ባምስት መቶ ሰው ድምጽ ተመረጥኩ" እያሉ ቀረቡ። ይህ አቀራረባቸው ያቡነ ማትያስን አደራራጊነትና አስደራጊነት ካቡነ ጳውሎስ ይልቅ እጅግ የባሰና የከፋ አድርጎታል።

፬ኛ:- በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት በተከሰተው ችግር አጥፊው በጽሑፍና በሰው ማስረጃ ቀረበላቸው። "ይህን ሁሉ ጉድ ከፈጸመ በኋላ አሁንም ይቀድሳል? ብለው ጠየቁ። ሲረጋገጥላቸው ተደንቀው ወደ ቢሯቸው እንደተመለሱ ውሳኔ እንደሚሰጡ ተናገሩ። በገቡት ቃል ጸንተው ውሳኔ ሊሰጡ ቀርቶ እንዲያውም ካቴድራል ብለው በሰየሙት በዋሽንግተን ዲሲ ቅድሱ ሚካኤል ቤተ መቅደስ ገብቶ እንዲቀድስ አደረጉ። ከዚያም መነኩሴ ቆሞስ ተብሎ እንዲሰየም አስደረጉ። ቁምስና ድግስ ተደግሶ በይፋ በህዝብ እልልታና ጭብጨባ ሊሰየም ይቅርና ህዝባዊ ህልውና አልነረውም። ይህም ይታወቀ ዘንድ በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት በተዘረጉት የተልእኮ መዋቅር መጽሀፈ ቅዳሴያችን ያሉትንና መኖር የሚገባቸው ሲደረድር ባንዲት ቦት ቆሞስ የሚባል ነገር የለም።

ከዚህ በፊት በተለያዩ ድረ- ገጾች በሚል ርእስ እንደገለጽኩት፤ ቆሞስ አለ ቢባል እንኳ፤ የጳጳስ መቋሚያ ተሸካሚ፤ በራሱ ምንም ማድረግ የማይችል፤ በጳጳስና በገዳማት መካከል ቀንዲልና ሌሎችም ነዋየ ቅድሳት በማቀባበል የሚላላክ፤ ከጳጳሱ የተቀበለውን ምክር ለገዳማት የሚያደርስ፤ በሽምግልናው ባዳበረው ገዳማዊ ልምዱ በዚያው ባለበት ገዳም ተራ እያስገባ የሚያስነብብ አጋፋሪ እንጅ በአባ ፋኑኤልና በዛሬው ቆሞስ ታደስ መካከል የተደረገውን ቤተ ክርስቲያናችን አታውቀውም አትቀበለውም። [*በሰፊው መረዳት ከፈለጉ ይህን ሰንሰለት ይጫኑ።* ፈር የለቀቀ ቁምስና የቤተ ክርስቲያን አደጋ ]

ይህ ዛሬ በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በአባ ፋኑኤል መሪነት ተፈጸመ የተባለው ቁምስና፣ መላ ህዝበ ክርስቲያን ባወቀው ስህተቱ የተወገዘው ግለ ሰብ ይቅርና፣ በጳጳስና በገዳማት መካከል ለነበረ ግንኙነት ተልእኮና በጳጳስ አጃቢነታቸው ተመዝነው በረዝም ዘመን ባሳዩት ትህትና ብቁአን ናቸው ለሚባሉ ሰዎች እንኳ በዚህ መልክ ተፈጽሞ አያውቅም። ህዝብን ሀገርን ቤተ ክርስቲያንን እየጠሉ ማስጠላት። እየተጣሉ ለማጣላት፣ እየዘረፉ ለማዘረፍ ለማዘራረፍ፣ እየከሰሱ ለማስከሰስ ለማካሰስ፣ እያፈረሱ ለማስፈረስ ለማፋረስ ለማፈራረስ የተፈጸመ ደባ ነው። ይህ ሁሉ ደባ ህዝብን አገርንና ቤተ ክርስቲያንን የሚያናውጽ ሲሆን፣ የቅኔያቻችን አእማደ ምሥጢራት መለሰ ብለን እንድንቃኝ፣ ለቅኔዎቻችንም መሠረትና ምሳሌ አድርገን የምንጠቅሳቸው ነብያት የተናገሩትን እንድንመረምር አድርገውናል።

## የቅኔዎቻችን መሠረቶችና ምሳሌዎች

የአብነት መምህሮቼ እንደነገሩኝ፣ የቅኔዎቻችን መሰረታውያን ምሳሌዎች የነብያት፣ የኢዮብ፣ የሲራክ፣ የሰሎሞንና የዳዊት መጻሕፍት ናቸው። ጥሩ የቅኔ ሰው ለመሆን የነዚህን አንድምታ መማር አለበት" ብለው ይመክራሉ። በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ያድራጊያቸው የፈጣሪያቸውን እጅ እናያለን። ፍጥረታትም አድራጊያቸውን እያንጸባረቁ እርስ በርሳቸው ይደራረጋሉ ያደራርጋል ያስደራርጋሉ። የነዚህን አንድምታ ያልተማረ ሰው ልቀኝ ቢል፣ ቅኔው የስድስቱን አእማድ ይዘትና ቅርጽ አያሟላልም። ቅኔውም ካሉባልታና ከማጎዳዳት ከማጣላት ከማጠፋፋት አይላቀቅም" ይላሉ። አባቶቻችን ለምሳሌነት ከሚጠቅሷቸ ውስጥ አንዱ ዳዊት የተናገረውን እንመልከት።

ዳዊት "ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር"
ወግብረ ዕደዊሁ ያየድአ ሰማያት

ዕለት ለዕለት ትጎሥዕ ነቢበ
ወሌሊት ለሌሊት ታየድዕ ጥበበ" እያለ ተናገረ። ይህም ማለት "ሰማያውያን ፍጥረታት ስለ እግዚአብሔር ይናገራሉ። የጁ ሥራ የሆነ ምድራዊ ፍጥረት ሁሉ ለሰማያውያን ፍጥረታት በራሳቸው የሚነጸባረቀውን የተፈጥሮ ምሥጢር መልሰው በመንገር ተሰጥኦውን ይመልሳሉ። ቀን ለቀን ጥበብን ትተርካለች። ሌሊትም ለሌት ጥበብን ታወራለች" አለ። ቀጠለና "ውስተ ኩሉ ምድር ወጽአ ነገሮሙ ወእስከ አጽናፈ ዓለም በጽሐ ነቢቦሙ" (መዝ ፲፰፡ ፩—፬) አለ። ይህም ማለት" የፍጥረታት የርስ በርስ ንግግሮች ተፍለቀለቁ፣ ዓለምን ከዳርቻ እስካድራች ሸፈኑ" አለ። በመቀጠልም፣ "ፍትሑ ለእግዚአብሔር ጽድቅ ወርትዕ ኅቡረ፣ ወይትፈቶ እምወርቅ ወእምዕንቁ ክቡር፣ ወይጥዕም እምዓር ወሦከር" (መዝ. ፲) አለ። ይህም ማለት፦ በፍጥረታት ላይ የሚታዩት የቅኔ አእማደ ምሥጢር ህግ የማይፋለስ ሚዛናዊ ነው። ከክቡር ወርቅና ዕንቁ የሚመረጥ ነው። ከማርና ከስኳር እጅግ ይጣፍጣል አለ። ቅኔ ከዚህ ክልል ከወጣ፣ እንደ ወያኔ ቅኔ ለማርና ለስኳር ተቃራኒ አቃራኒ፣ መራራ አስመራሪ እሬት መሆኑ ነው

ሊቃውንት አበው ሊቅንያቸው ምሳሌና መሰረት አርገው ያቀረቡትን የዳዊትን አገላለጽ፣ ከዘመናውያን ጠበብቶች አንዱ Sherwin B. Nuland የተባሉ "The Wisdom of the Body" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው፣ ምሥጢራተ ፍጥረታትን እየተነተኑ መጥው ከሰባዊ አካል ቅንብር ላይ ሲደርሱ "By an extraordinary system of messages transmitted by hormones and nerve impulse, the various structure of the body make known thier moment to moment needs"(35) ሲሉ ገለጹት። ይህም ማለት የሰውነታችን ቅመማት፣ ስሜቶቻችንና ትርታ፣ ቅጽበትዊት የሆነችውን ፍላጎታቸውን እጅግ በሚያስደንቅ ፈሊጥ (ቅኔያቸው) ይለዋወጣሉ ይነጋገራሉ። ይህን ማድረግ ከሳቱ ታመዋል ተናውጠዋል በመሞት ላይ ናቸው። በመጨረሻም በነሱ ውህደት የተገነበው ሰውነት ይሞታል ማለት ነው ። ቋንቋዎቻቸውንም biospeake ብለውታል።

እንደዚሁ ሁሉ የተለያዩ ጎሳዎች፣ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና የነበሩት ጥንታውያን እምነቶች ማለትም የይሁዲ የኦርቶዶክስ ክርስትናና የእስልምና እምነቶች ያንዲትን ኢትዮጵያ የሰሩ ናቸው።በተቀነባበሩባት ባንዲት አካላቸው ውስጥ ሆነው ከዘመን ዘመን፣ ከትውልድ ትውልድ፣ እየተሸጋገረች ከዚህ ለደረሰችው ኢትዮጵያ ሙሉ አካላት ናቸው። በወለደቻቸው እናቸው ችግር ሲፈጠር ሁሉንም ይነካቸዋል። መነጋገር መወያየት አለባቸው። ይህን እንዳያደርጉ የመተርጎሙ አቅሙ ሽባ የሆነ ወያኔን የመሰለ መሪ ሲገጥም ህዝባዊ ራእይ በደመና ይሸፈናል። ይህንንም ለማስረዳት እኚሁ ሊቅ "How can moral imagination be attained when the subject is someone whose intrpration of his surounding is clouded by the guazy veil of mental retardation? (Page 142) ሲሉ ተናግረውታል። ማለትም፦ ተርጓሚና በተግባር የሚያውለው ሰው መንፈሰ ሽባና አተረጓጎሙና አሰራሩ በጥቁር ደመና የተሸፈነበት ወያኔን የመሰለ ደካማ ቡድን መሪ ከሆነ፣ የሞራል ትክክለኛና ሚዛናዊ ግምት እንዴት ማግኘት ይቻላል?

ከላይ እንዳየነው፣ ዳዊት የፍጥረታትን ንግግርና ስሜት መቀባበል እያብራራ መጥቶ፣ በወያኔ አመራር አይነት ያለ ህዝብ ያለፋታ በላው ላይ የሚጎርፍበትን አሳሳች ነገር ለመያት የሚችሉ ብርሁ ጭንቅላት ያላቸው ሰዎች ቁጥር አንስተኛ መሆኑን ለማሳየት "ለስሂት መኑ ይሌብዋ" ሲል ከተናገረው ጋራ የNuland ንግግር ገጠመ።

ነቢዩ ዳዊት በተፈጥሮ ቅኔ ያሉትን አዕማደ ምስጢር በተዘበራረቁበት ህብረተ ሰብ ውስጥ አራሚና አስተዋይ እንደሌለ ታዝቦ "ለስሂት መኑ ይሌብዋ" ብሎ በመጠየቅ አላቆመም። ወደ ራሱም መለስ አለና፤ "እመሰ ኢቀነዩኒ ውእተ ጊዜ ንጹሐ እከውን" (መዝ ፲፫) ማለትም፦"በቅኔ አዕማደ ምሥጢራት ተቃራኒ መንገድ የማልሄድና ለነሱም መንፈሴን ካላስገዛሁ ከመንፈሰ ሻባነት የተገላገልኩ፤ በልዕለ አዕምሮ የጸዳሁ ነኝ" እያለ ተናገረ።

የቅኔ መምህራን እንደሚሉት፤ ህጻን በተፈጥሮው የእሬትን ምሬትና የማርን ጣፋጭነት በመቅመስ ለይቶ እንደሚያውቅ፤ ማንም ሰው የቅኔን ይዘትና ለዛ ህብሩን ሰምና ወርቁን ተርጉሞና አብራርቶ መግለጽ ባይችልም፤ በተለይም በአዘማሪ ሲቀርብ በቅኔ የሚገለጸውን የተፈጥሮን ውበት የሚያደንቅበት ስሜትና መጠነኛ እውቀት አለው። ስለዚህ እነዚህን አእማድ ሳያውቅ ማንም ሰው ከድርጅታዊ አሰራር መግባት ይቅርና ከትዳር መግባት የለበትም ይላሉ አባቶች። "የቅኔን አዕማድ መረዳት አቅም የሌለው ሰው ትዳር፤ ማህበር፤ ድርጅትና አገር ለመምራት በግንባር ቀደምነት ሲሰለፍ፤ ትዳር፤ ማኅበር፤ ድርጅትም ይቃወሳልል። አገር ይናወጣል። ዳር ድንበር ይፈርሳል። ህዝብ ይታመሳል። ለዚህም ያብነት መምህራን የነቢዩ የናስን ህይወት እንደ ምሳሌ አርገው ያቀርቡታል። ዮናስ በመርከብ ውስጥ ገባ። ወደ ሚናወጠው ባህር ተወረወረ። አሳ አንባሪ ዋጠው። በአሳው ሆድ ሆኖ እመቀ እመቃት ወረደ። ወደ ጥልቀቱ ገባ። አየረ አየራት ወጣ። ማእበሉ ጎርፉ ሁሉ በሱ ላይ ሄደበት። ከዚያ በኋል የሚከተለውን ተናገረ።

# የዮናስ ንግግር፦

"እመኒ ወረድኩ ውስተ ቀላይ ህየኒ ሀሎከ፤ ወእመኒ አረጉ ውስተ ሰማይ ህየኒ ነበርከ።ወወረድኩ ውስተ ምድር ከመ መልህቅ ታህተ። ኩሉ ማእበልከ ወሞገድከ እንተ ላዕሌየ ሐለፈ" (ትንቢተ ዮናስ ምዕ ፪ ) ማለትም፦ "ወደ ሰማይ ወጣሁ በዙፋንህ እንዳለህ ተረዳሁ፤ እመቀ እመቃት ወረድኩ፤ እዚያም አንተ አለህ። የስነ ፍጥረትህ ጥልቀት፤ ምጥቀትና ስፋት ማእበል ሆኖ ጭንቅላቴን አናወጠው" አለ። አባቶቻችን የቅኔ መምህራን እንዳሉት የቅኔ ሰው ምርምሩን ከራሱ ከሰውነቱ ከሱነቱ ካካባቢው ይጀምራል። ይህም አባባላቸው ከላይ ስማቸውን የጠቀስኩት የዘመኑ ሊቅ "our cells live not in the air through which we wallk, but in the fluide in which they are bathed (32 ) ሲሉ ከተናገሩት ጋራ ተስማማ። ይህ አባባላቸው፤ ተወልደን ወደ ዚህ ዓለም ከመጣንባት ቅጽበት ጀምረን እስከደረስባት ቅጽበት የከባቢውን አየር ማእበል እየቀዘፍን መኖራችንን ብቻ ሳይሆን፤ ገና ስንጸነስ ህይወታችንን በነውጥ ማእበል እንደ ጀመርነው ያሳያሉ። ስለዚ የቅኔ ሰዎች፤ የቅኔን አእማደ ምስጢራት በተረዱት አመራር ስር በመሆናቸው "ምስለ ዘይትፌሣሁ ተፈሥሑ" ደስ ብሏቸው ከሚስቁት ህዝቦች ጋራ ይስቃሉ። "ወምስለ ዘይበክዩ ብከዩ"(ሮሜ ፲፪ ፡፲፭) በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ነውጥ ሆነው ከሚያለቅሱት ጋራ ያለቅሳሉ። እንደተባለው" የቅኔ ሰዎች ጠቅላላው ህዝባቸው ደስ ሲለው ደስ ይላቸዋል። ሲከፋው ይከፋቸውል።

ነቢዩ ዮናስ "እለ ይትላጸቁ ምስለ ከንቱ ሀጥኡ ህይወቶሙ ወጠፍኡ ምስለ ጣዖቶሙ (፰ ) እንዳለው፦ አገርን ድንበርን መንደርን በማፈራረስ ህዝብ የሚናውጹ ሁሉ ይጠፋሉ። በማፈለስና በማናወጥ ማእበል በመሳተፍ ላይ ያሉትን ሰወች ሁሉ አብረው እንዳይጠፉ ይመክራል። ነቢዩ ዮናስ "ትዕርግ ሕይወትየ ዘእንበለ ሙስና ኀቤከ እግዚኦ አምላኪየ" እንዳለው። ሁሉንም አየሁት፣ ታዘብኩት በስነ ፍትረትም ረካሁ፣ ሰከንኩ፣ ያላንዳች ውድቀትና ጉድለት ነፍሴ ወዳንተ እንድትምጣ እመኛለሁ" ብሎ ቅኔውን ደመደመድማል።

የተፈጥሮ ሳይንስ ሊቅ ነበር ተብሎ የሚነገርለት ቅዱስ ባስልዮስም "ቦኑ ይትከሀለነ ንጠይቅ ስፍሀ ሰማይ ወእመቀ ቀላይ እመሰ ኢንክል ንጠይቅ ኅዳጠ እምፍጡራን እፎኑመ ይትከሀለነ ንብጻህ ኀበ አእምሮ እግዚአብሔር "((ሃ አ ፴፫፡፲፪)) ብሎ የተናገረውን ይጠቅሱታል። ማለትም፦ በቅኔያችን ሀሳብ እመቀ እመቃት ብንወርድ፤ አየረ አየራት ብንወጣ የፍጥረትን የምሥጢር ስፋትና ጥልቀት መረዳት ያዳግታል። ይህ ካዳገተን ከፍጥረት ባለቤት ከፈጣሪ ዘንድ መድረስ እንዴት ይቻላል? አለ። ቀጥሎም "ረኀቅ እምነ ምድር ወተልዓል እምነ ባሕር። ወዕርግ መልዕልተ ዓየር አዕምር ውላጤ ሰአታት። ፍጡነ ወሠርጎ ከዋክብት ወኀድግ ኩሎ ፍጡራነ እለ ውስተ ምድር"( ፲፮) በዚህ ዓለም የሚደራረገውን የሚጎዳዳውን የሚሳመጠውን ተወውና ከሚደረገው መሳመጥ ውጣ። በሰዓታት የሚከናወኑትን የከዋክብትን ውበት ተመልከት ከልዕለ አእምሮ እርከን ላይ ለመድረስ በርትተህ ጣር " ይላል። ሰው ስለሚበላው ስለሚለብሰውና ስለሚኖርበት ቤት ብቻ በማሰብ ሰአቱንና ዘመኑን ከፈጸመ፤ በፊታቸው ያለውን ሳር እየነጩ ገደል ከሚገቡ እንስሳት የተሻለ አይደለም።

Nuland የተባሉ ሰው "No matter how simililar our parts to those of other animals, there are to be found within them some characteristics that make us uniquely humam". እንዳሉት፦ በለበስነው ሥጋችንና ፈቃደ ሥጋችን በደመ ነፍስ ከሚንቀሳቀሱት ዘንዶዎችና እባቦች ከሌሎችም እንስሳት ጋራ ብንመሳሰልም፤ ከሚታየው ከሚዳሰሰው ከሚበላው ቁሳቁስ ላይ ዓይናችንን አንስተን በተገቢው መንገድ እንድነገለገልባቸው በቅኔዎቻችንን አዕማደ ምሥጢራት ላይ ማተኮር አለበን ብለው ኢትዮጵያውያን የቅኔ መምህሮቻችን ያስገነዝቡናል። ከዚህ ቀጥየ ወደ አዘማሪ እሻገራለሁ።

# አዘማሪ

ከመግቢየ ላይ እንዳልኩት የዚህች ጦማር መነሻ በየነጻነት ሬድዮ አቶ ዓለም በሚያቀርቡበት ሰአት “የቱ ቃል ነው ለባለሙያዎች ተስማሚ መገለጫ መሆን ያለበት? አዝማሪ ወይስ አርቲስት? የሚል አጠያያቂና አነጋጋሪ ቀርቦ ነበር። ስለዚህ ነገር የሰማህው ነገር ካለ አካፍለን የሚል ጥያቄ ስለቀረበልኝ ለዚህች ጽሑፍ መነሻ ሆኖኛል። የቃሉ ምንጭ “ዘመረ” የሚለው ነው። ዘመረ የሚለው ቃል አድራጊን በዘማሪውና በመዝሙሩ ላይ ብቻ ይወሰናል። አዘማሪ የሚለው ቃል ደግሞ ተሸጋጋሪ (አደራራጊ) ነው። ማለትም የተፈጥሮ ውበት የሚያንጸባርቀውን ፈጣሪን እያመሰገነ የህብረተ ሰብን ስሜት በስድስቱ አእማደ ምሥጢራት ስልት ማስተባበሩን ማዋሀዱን ማቀራረቡን ማስማማቱን ያመለክታል። አዘማሪ በስድስቱ አእማዶች ተቀረጹትን ቅኔዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ባህላውያን የዜማ አይነቶች አለብሶ በጉሮሮው ቅላጼ ከመሰንቆው፤ከክራሩና ከበገናው ጋራ በማስማማት በማቅረብ የሰሚውን መንፈስና ስሜት ህሊና በፍቅር በጨዋታ በሳቅ በፈገግታ እያቀራረበ የሚያኳሽ ነው። ወቅት በመጠበቅ በሀዘን በደስታ በጦርነት ጊዜ መቅረብ ያለባቸውን እያቀረበ ይመራል። ብዙ ተሻሚና አሻሚ ያለውን አርቲስት የሚለውን ባእድ ቃል ከመሸከም ይልቅ አዘማሪ የሚለውን ባይለቅ ኢትዮጵያዊውን ውበት ሳያፋልስ ይኖራል ብየ እገምታለሁ።

ከዚህ በማስከተል አቅሜ የፈቀደልኝን ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች ወይም ግጥም ለአዘማሪ በሚመቸና፤ ማንም ሰው በሚረዳው መንገድ በግእዙ ከምንቀኘው የቅኔ ደረጃ በጣም ዝቅ በማድረግ የራሴ ቅኔ አቅርቤያታለሁ። በቤተ ክርስቲያናችን ሥርአት ቅኔ በሁለት ክፍል ይዘጋል። የመጀመሪያው ክፍል የዕለቱን በዓል ያንጸባርቃል። ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ‘ለዓለም (አሰረ ንጉሥ) የሚል ስም ተሰጥቶት፤ መሪወችንና ያካባቢውን ሁኔታ ይዳስሳል።

ለውጩ ዓለም ትምህርት ከኢትዮጵያ ሳልወጣ በካህናት ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት በማስተምርበት ጊዜ ፤ የንጉሡ ሥርአት ከፈረሰ በኋላ፤ በንጉሡ ዙሪያ ይባሉ የነበሩ ሁሉ በኢትዮጵያና በህዝብ ሲተኩ በቅኔያችን የነበረው አሰረ ንጉሥ የሚባለውም ክፍል፤ በህዝብ እንዲተካ ኢለቃ ነቢየ ልዑል፤ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ፤ መሪጌታ በላይ ውብሸት፤ መላከ አርያም ይትባረክ መርሻ፤ መርጌታ ልሳኑና በመጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል በሚወያዩበት እድል ገጥሞኝ በውይይቱ ተካፍያለሁ። በኢትዮጵያ ያሉ መምህራን ምን እንደሚሉት አላውቅም። ይህችን ግጥም (ቅኔ) ሳቀርብ መነሻ ያደረጉት በዕለታዊ በዐል ቦታ የራሴን ስሜት፤ በአሰረ ንጉሥ ቦታ በዚህ ወቅት በአገር በቤተ ክርስቲያንና በጠቅላላው ህዝብ ላይ ያተኩራል ብየ የገምትኳትን ሁሉ በመዳሰሰ ለምሳሌ ያህል የራሴን ግጥም ወይም ቅኔ ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

## ለምሳሌ ያቀረብኩት ቅኔ ወይም ግጥም

ብሶቴን ጭንቀቴን ልጆቼ ቢረሱ
የምጽፍባቸው ብእሮች አለቀሱ
የኔ ሲያልቅባቸው እንባ እየተዋሱ።

መፎከር አይችሉም አያውቁ ቀራርቶ
ምነው ባልሳቁብኝ መፈከሩ ቀርቶ

በማንበብ ላይ ሳለሁ መጽሐፍ ዘርግቼ
በመጽሐፉ ላይ ፈሰሱ እንባዎቼ።

የያዝኩትን መጽሀፍ ገልጩ ሳየው
ለይቶ ለማንበብ ዓይኔን አቃተው
የጎረፈው እንባ ፊቴን ሸፈነው።

በንባዬ ስበሳጭ በፈሰሰው ከዓይኔ
ሆኖ ተረዳሁት ደምሳሹ ወያኔ።

ቁጭ ብየ ኣላለቅስ ወንድ አርጎ ፈጥሮኛል
ተንበርክኬ አልተኩስ ቀሲስ አድርጎኛል
ሰላም ሳይኖር ሰላም፤ ማለት ሰልችቶኛል።

የዘመኑ ነገር ግራ ያጋባኛል
ከመቀኘት በቀር፥ ምርጫ አሳጥቶኛል።

የዘመኑ ግጥም፡ ቅኔው የገባችሁ
መረዳት አቃተኝ፡ እርዱኝ እባካችሁ
ትርጉሙን ንገሩኝ፡ አንድም እያላችሁ።

በኪንሳስ ከተማ፡ በመሰረትኳት
በቨርጅንያም ላይ ቆሜ ያየሁት
ሁሉም አንድ ናቸው ኪደነ ምህረት
የጌታች እናት እሷ ናት በውነት?

ወንደ ላጤ ሁሉ ሲነግድባት
እንዴት ረሳቸው ታምር መስራት
ያደረገችውን በነዳጎን ቤት።

ቀርቤ ያየሁት ተመሳሰለብኝ
ውሸቱ ክደቱ አንድ አይነት ሆነብኝ።

ይህን ስለጠየኩ ሳልፈራ ደፍሬ
መናፍቅ ነው ብለው አወሩብኝ ወሬ።

ክርስቲያኖች ሆይ በጣም ተጠንቀቁ
እውነቱን መስክሩ ማነው መናፍቁ
ሀሰት መናገር ነው ወይስ መጠየቁ?
ከእንዲህ ያለ ቦታ አትቅረቡ እራቁ!

አያጸድቃችሁም አብሮ መጓተቱ
ይልቅስ ለማወቅ ለመረዳት በርቱ።

ኃይለ ማርያም ገብቶ፡ ከወያኔ ማበር
ከመለሰ ጽዋ ተቀብሎ ነበር።
አላውቅበት ብሎ፡ ማለት ባለ ሳምንት
በራሱ ልብስ ላይ፡ ወይኑ ተደፋበት።

አሁን ባጭር ጊዜ፡ አየዋለሁ ባይኔ
እያለ ሲያለቅስ፤ አዬ ወይኔ አይ ወይኔ።

ጠላ የጠጣ ሰው አያገሳም ጠጅ፤
ሰው አይወቀስም፡ ያለ አንዳች አስረጅ።

ምንይልክ ጥም እንጅ፡ የሰው ጡት
አይቆርጥም
መቁረጥ ይቅርና፡ ሰምቶትም አይውቅም።

ባይሆን የሚታማው ዮሐንስ ነው እንጅ
በሰይፍ በመቁረጡ የስላሞችን እጅ።

መውጣት ያቃታቸው ከጭለማ አረንቋ
ጡት ቆራጭ ይሉታል በራሳቸው ቋንቋ።

በራሳቸው ተግባር በሰሩት ስራቸው
ጡት ቆራጭ ይሉታል በዚያው
በቋንቋቸው።

ከታላላቅ ሰዎች እኔ እንደ ሰማሁት
እናት ለሌላቸው የሚጠቡት ላጡት
እረፍት ሳይሻ ያድል ነበር ወተት።

እጅግ የረቀቀ ምንይልክ ሊቅ ነበር።
ገለልተኛ ሆኖ አንድ ዘር እንዳይቀር
በኢትዮጵያ ውስጥ ባንዳ እንዳይፈጠር።
አንዱን ዘር ከሌላ ይቀላቅል ነበር።

እነ አቶ መለሰን እንዴት አመኗቸው?
ምን ይልክ ቆራጭ ነው ብለው ሲነገሯቸው።
ቢሰልሏቸውን በጣም ቢንቋቸው።

እውነቱን ንገሩት ለስብሀት ነጋ
ሀሜቱን እንዲያቆም መብላት የሰው ሥጋ።
የሚጨነቀውን ለወገን ለዜጋ
መክሰሱን እንዲያቆም አፉም እንዲዘጋ
ከምንይልክ ይሽሽ ይራቅ አይጠጋ
ወሰን ድንበር ሲፈርስ የጥንቱ ሲናጋ
ጠበል ይረጭ ነበር ሕዝብ እያረጋጋ።

ምን ይልክ ቅዱስ ነው በሥጋ በነፍሱ
ሁሉን የሚበላ አይደለም እንደሱ ።

ምን ይልክ ቅዱስ ነው አይደለም ርኩስ
ጠበል እየረጨ ሁሉን የሚቀድስ።

የሀብተ ጊዮርጊስ ዘሮች የሆናችሁ
ያለፈውን ታሪክ ተረዱ እባካችሁ
ምን ይልክ ጡት ቆራጭ ማለቱን ትታችሁ
ገብረ ኪዳን ደስታን አንቃችሁ ይዛችሁ
በቁጻር አጥምቁት እያናዘዛችሁ
እንዴት እንደዋሸ እንዳታለላችሁ።

የወያኔ ቁሶች ወያኔ አለቃቸው
አገር እንዲያፈርሱ ያሰለጠናቸው
በታትኑ ከፋፍሉ ብሎ የላካቸው

የማያምኑ ናቸው በድሜ ያልቀመሱ
የቁሶችን ውግዘት ትዳር አፈረሱ።

እሱ በካናቸው በወጉ በልምዱ
እያፈረሱ ነው ልጆች የሚወልዱ።

ወንበዴ አመንኩስህ ይቅርብህ መላኩ
ይልቅስ ገለል በል ወግድ ከመድረኩ
አገልግል ሴቶችን በወጉ በመልኩ
ቀሚስ እየሰፋህ ለሁሉም በልኩ።

አዲስ ተክል መሆን ይህ ነው ውጤቱ
የተጻፈውን ህግ ለወንዱ ለሴቱ
ወያኔ አበላሸው አደረገው ከንቱ
ክብሩን ዕልልታውን አፋልሰው ከጥንቱ
ለታደሰ ሰጡት ነጥቀው ከታቦቱ።

የዘመኑ ሴቶች ምነው ተሳሳቱ
ህግ ላፈረሱ ደፍረው ተሟገቱ።

የዘመኑ ሴቶች ተማሩ እባካችሁ
ሰይጣን ረቂቅ ነው ከሄዋን ለያችሁ
በጣም ዓይነ አፋሮች ቀድሞ ነበራችሁ
አይነ ጥላ ገፎ አሰለጠናችሁ
ላስመሳይ መነኩሴ ጠበቃ አረጋችሁ።

ለፋኑዔል ቆሞስ እልል ማለታችሁ
ያስኮንናችኋል እንኳን ሊያጸድቃችሁ።

ዘመናን የፈጀች ብኩና ማርታ
ለከንቱ ውዳሴ መሯሯጥ አብዝታ
ብዙ አትሩጭ ብሎ መክሯት ነበር ጌታ።

ለጠቀሚ ነገር በርትታችሁ ሥሩ
በማርታ መንፈስ ሳትሰሳሰሩ።

በወዳጅ በጥቅም ሆነና ነገሩ
ለቁምስና ደግስ ሰዎች ተጠራሩ።

እንደ እነ ፋኑዔል የመነኮሳችሁ
መናገር አትችሉም አይጥምም ግጥማችሁ
አትሞክሩ ቅኔ ያለችሎታችሁ
መቁጠር ሳትማሩ ይቅር ዘረፋችሁ።

ካህናት አይደሉም የቆመሱ ናቸው
ካራሷ ሴት ሳይቀር ንክኪ ያላቸው
አትጠጉ ሴቶች በሩቁ ሽሿቸው
አባራቸው እንጅ ባርኩን አትበሏቸው።

ወደ አባ መላኩ ቀርበው የቀሰሱ
አጸያፊ ናቸው ሁሉም የረከሱ
ካፈረሰው ጋራ ተባብረው ቀደሱ።

አንዳርጌ ይቅርብህ ወደ አገር መመለስ
አውሬ ወደ ዱሩ እስኪመለስ ድረስ።

ቀኑ ገና አልነጋም ድቅድቅ ነው ጨለማ
ኢትዮጵያ ሆናለች የአራዊት ከተማ

እኒህ አራዊቶች ዱር የወለዳቸው
የሰው ደም መጠጣት ሥጋ ነው
ምግባቸው።

ከወያኔ ድግስ ራቁ አደራችሁ
የሰውን ሥጋ ነው የሚያቀርቡላችሁ።

በውነት አርበኛ ነው ጀግናው አንዳርጋቸው
በወያኔዎች ላይ ተጫወተባቸው
በሩቁ ሆኖ ሲያዩት የሸሸ መስሏቸው
ለጨበጣ ውጊያ ገባ ከጉያቸው።

አዬ ዬ ኢትዮጵያ የጋባቸው ጣጣ
ከሚንጋጋው ሁሉ አንድ ጳጳስ ትጣ
በገዳም የሚቆይ ከዋሻ የማይወጣ፤
በቆቡ ላይ ጤፉን ተሸክሞ መጣ።

አንዳርጋቸው ጽጌ ታማኝ ነው በእውነት
ከወገን ጋራ አብሮ መብላት መጠጣት
ከባድ እንድሆነ ነገሩ ገብቶት
ተመልሶ ገባ አብሮ ለመሞት።

ማር ይሳቅን ስማ አንተ ያገሬ ሰው
ቆቡን ባጠለቀ የምትታመሰው።

መነኩሴ ነው ብለህ ቃሉን እንዳትሰማ።
ምንኩስናው ቀርቷል ሲገባ ከተማ።

መነኩሴ ተዝናንቶ ሲበላ ሲጠጣ
ባላገር ተከዘ አዘነ ተቆጣ
ቆሞ እያለቀሰ ተዝካሩን አወጣ።

ራስህን ፍታ ከወያኔ ገመድ
ምንኩስናን ክደህ ዓትገዛ ለሆድ
እየታዘበህ ነው ሁሉም ወዳጅ ዘመድ።

አንዳርጌ መነኖ ከትዳሩ ሲርቅ
ቆሞሱ ተያዘ የሰው ሚስት ሲሰርቅ።

እምነቱን ጠባቂ ጽኑእ ኦርቶዶክስ
በምንኩስና ስም ገብቶ ሲቀድስ
መቅደሱ ሲቃለል ቁርባኑ ሲረክስ

ቆራቢ አስቆራቢ ጳጳሱ ሲስማማ፤
ይህን እንዳያይ ይህን እንዳይሳማ፤
አንዳርጋቸው ሸሸ ወጣ ከከተማ።

ቃል ኪዳኑን ቢክድ መነኩሴ ተታሎ
ሁሉም ሊመንን ነው አንተን ተከትሎ።

እንደ ሸቀጥ እቃ እያገላበጡ
እነ አባ ማትያስ ዜግነት ሲሸጡ
ሁሉን ንቆ ተወው አንድ አርጌ ቆራጡ።

ዜግነቱን ሲሸጥ መነኩሴ ለሹመት
አንዳርጌ እጁን ሰጠ ላመነበት ሊሞት።

እስቲ ተመልከቱ ይህ ነገር አይደንቅም?
መነኩሴ ሲሳመጥ ለሹመት ለጥቅም?
አንዳርጋቸው ጽጌ ላመነበት ሲቆም?

አረም ወራሪ ነው ሳይዘራ እሚበቅል
መታረም ያለበት ከስሩ መነቀል።

ወራሪው ወያኔ ገብቶ በሰው ማሳ
የመሬቱን ድንበር ለማፍረስ ተነሳ።

የሚታረመውን እንክርዳዱን ትቶ
ንጹሁን ቡቃያ ይነቅላል በርትቶ
ዘር ማጥፋቱ አይቀርም ቆይቶ ቆይቶ።

ከሀሰት ፈልቅቆ እውነት የሚያወጣ
የእውነት ነጸብራቅ ነበረ ጋዜጣ።

ራሱ እየዋሸ በሰው ያመካኛል
የሰዎች ቅጥረኛ ታዛዥ ነኝ ይለኛል።

እውነት ፈላጊ ነው ጥሩ ጋዜጠኛ
ራሱን ያስገዛል ለህሊናው ዳኛ።

በጋዜጠኛ ስም ሰው የሚያታልሉ
ስንት የታዘብናቸው ጋዜጠኞች አሉ።

በደዌ በርጅና በሚሞት ሥጋችሁ
አረመኔው ምንግሥት ወያኔ ቢያስራችሁ
በሰማይ በምድር ነጻ ዜጎች ናችሁ።
ታራሚው ወያኔ ታራሚ ቢላችሁ
እንዳትቀበሉት እውነት ነው መስሏችሁ
ባመናችሁበት ቁሙ ጠንክራችሁ
አንዳርጋቸው መጥቷል ሊተባበራችሁ።

ምሳሌዎች ናችሁ ለዘመኑ ትውልድ
እናንተን ሊከተል ሁሉም ወዳጅ ዘመድ
ተሰልፎ ቆሟል ሊጀምር ነው መንገድ።

ምንም ባላምንበት በእስረኝነታችሁ
ይላል ቅስናየ እግዚአብሔር ይፍታችሁ
በአካል ርቄ ይህንን ስላችሁ
ምንግዜም በነፍሴ አለሁ አብሬያችሁ
እያለቀስኩ ነው ስሰናበታችሁ።

ይቆየን::